የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፮
አዲስ አበባ ግንቦት ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፪

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

6th Year No. 36
ADDIS ABABA - 6th June, 2000


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፪፻፮/፲፱፻፺፪ ዓ.ም.
የዕፅዋት ዘር አዋጅ .................................. ገጽ ፩ሺ፫፻፲፯


### አዋጅ ቁጥር ፪፻፮/፲፱፻፺፪
### የዕፅዋት ዘር አዋጅ

ኢትዮጵያ ባላት ሰፊ የመሬት ክልልና የተለያዩ ስነምህዳሮች የልዩ ልዩ ዓይነት የዕፅዋት ዘሮች መገኛ በመሆን ወይም ከውጭ የመጡ የተለያዩ የዕጽዋት ዘሮች በቀላሉ በሚላመድባቸው ለእርሻ ተስማሚ በሆኑ ልዩ ልዩ ስነምህዳሮች የታደለች በመሆኗ፣ የዕፅዋት ምርትም ለሀገሪቱ ኢኮኖሚና ለአብዛኛው ሕዝብ ኑሮ የጀርባ አጥንት ሆኖ በመቆየቱና ወደፊትም የሚቀጥል በመሆኑ፣

የዕፅዋት ምርትን ለማሳደግ ከሚያስችሉ ዘዴዎች መካከል ዋነኛው አርሶ አደሩ ጥራቱ የተጠበቀ ዘርን በተለይም የተሻሻሉ ልዩ ልዩ ምርጥ የዕፅዋት ዘሮችን እንዲጠቀም ሲደረግና እነዚህን ዘሮች በቀላሉ እና በተቀላጠፈ መንገድ የሚያገኝበት ሁኔታ ሲመቻች በመሆኑ፣

ጥራቱን የጠበቀ ዘር ለአርሶ አደሩ የሚደርስበትንና ምርጥ ዘር በስፋት ሥራ ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ለመፍጠር እና ለዕፅዋት ዘር ተጠቃሚዎች እና አምራቾች፣ አዘጋጆች፣ አከፋፋዮችና ቸርቻሪዎች ጥቅም የሕግ ጥበቃና ቁጥጥር የሚደረግበትን ሁኔታ የሚያረጋግጥ ሥርዓት ማስፈለጉ ግንዛቤ ያገኘ በመሆኑ፣

ምርጥ ዘር የሚያመርቱ፣ የሚያዘጋጁ፣ ወደ ውጭ የሚልኩ፣ ወደ አገር ውስጥ የሚያስገቡ፣ የሚሸጡና የሚያሰራጩ ግለሰቦችን (ድርጅቶችን) የሚያግዙ ፣ የሚያማክሩ እና የሚቆጣጠሩ መንግሥታዊ አካላትን መሰየም በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የዕፅዋት ዘር አዋጅ ቁጥር ፪፻፮/፲፱፻፺፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## CONTENTS


Proclamation No. 206/2000
Seed Proclamation .................................. Page 1317


### PROCLAMATION NO. 206/2000
### SEED PROCLAMATION

WHEREAS, Ethiopia, within its territory of vast land mass, and a microcosm, is endowed with a variety of agro-ecological zones which made possible for a great diversity of crop species to originate, or, least, to grow and perform as nicely as they do in their home areas, and crop production has been and will certainly continue to be the backbone of the country's economy and the livelihood of the great majority of the Ethiopian population;

WHEREAS, one of the most effective means of achieving increased crop production is enabling farmers to use high quality seed particularly of improved crop varieties and making such seeds available as smoothly, effectively and quickly as possible;

WHEREAS, realizing the need for creating conducive conditions for the distribution to the farmers and the wide utilization of quality seed; and the need for creating a legal framework for the protection and control of the interests of users, originators, processors, wholesalers, and retailers of plant seeds;

WHEREAS, it has been necessary to designate governmental bodies which support, advise and control individuals/organizations engaged in production, processing, import, export, sale and distribution of quality seeds;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### PART ONE
### *General*

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Seed Proclamation No. 206/2000"

፪· ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡

፩· "ቦርድ" ማለት የብሔራዊ ዕፅዋት ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ ቦርድ ነው፡

፪· "ኤጀንሲ" ማለት ብሔራዊ የዕፅዋት ዘር ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ ነው፡

፫· "ዝርያ" ማለት የማናቸውም ዕፅዋት ቤተሰብ ሆኖ፣ ከሌሎች ዝርያዎች በግልጽ የሚለይበት ተወራራሽ የሆነ መለያ ባሕርያት ያለውና በዘር ፍሬም ሆነ በሌላ መንገድ ሲባዛ ባሕርያቱን የማይለውጥ የዕፅዋት ዘር ነው፡

፬· "ዘር" ማለት እውነተ ዘር፣ አኩራች፣ ቅጥፍ ተክል፣ የማሳ ሰብሎችና የጓሮ አትክልት ችግኞች ወይም ለዕፅዋት ማራባት የሚያገለግል ማናቸውም የተክል ክፍል ወይም አካል ነው፡

፭· "የተደነገገ ዘር" ማለት የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ የሚሆኑበትና ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ዘር ነው፡

፮· "የተመሰከረለት ዘር" ማለት በአገር ውስጥ የተመረተ ወይም ወደ አገር ውስጥ የገባ አስፈላጊዎቹን የኢትዮጵያ የዘር ደረጃዎችና መስፈርቶች ማሟላቱ በኤጀንሲው ወይም ይህንን ሥራ ለማከናወን በኤጀንሲው በተወከለ ሌላ አካል የተረጋገጠለትና ለዘርነት የሚውል ዘር ነው፡

፯· "አፅዳቂ ኮሚቴ" ማለት ብሔራዊ የዕፅዋት ዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ነው፡

፰· "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡

፱· "የዘር መረጃ ማዕከል" ማለት የብሔራዊ ዕፅዋት ዘር ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ የዘር መረጃ ማዕከል ነው፡

፲· "የኢትዮጵያ የዘር ደረጃዎች" ማለት በኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን የወጡ የዕፅዋት ዘር ደረጃዎች ናቸው፡

፲፩· "ጥራት" ማለት የተደነገገው ዘር ለዘርነት ያለው ብቃት ነው፡

፲፪· "ውግዝ የአረም ዘር" ማለት በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ተለይቶ የታወቀ ልዩ የአረም ብቸኛ ዝርያ ዘር ነው፡

፲፫· "ምልክት" ማለት ማናቸውም በዘር መቋጠሪያ ላይ የሚደረግ ወይም የሚያያዝ ወይም ከዘር ጋር የሚሔድና የዘሩን ጥራትና መጠን ለመግለጽ የሚያገለግል ማብራሪያ ምስል ወይም ንድፍ ነው፡

፲፬· "የዘር ማዘጋጃ ቦታ" ማለት ለዘር ማዘጋጃ እንደአስፈላጊነቱ ለማድረቅ፣ የማይፈለጉ ነገሮችን ከዘሩ ውስጥ ለማስወገድ፣ በመጠን ለመለየት፣ በመድኃኒት ለመለወስ፣ ለማሸግ፣ በቂ ዝግጅትና ማከማቻ ቦታ ያለው ነው፡

፲፭· "የተገደበ ዘር" ማለት ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ ወይም ከኢትዮጵያ እንዳይወጣ የተከለከለ ወይም ገደብ የተደረገበት ዘር ነው፡

፲፮· "ደረጃ ያላሟላ የዕፅዋት ዘር" ማለት የኢትዮጵያን የዘር ጥራት ደረጃ መስፈርቶች ያላሟላ ማንኛውም የዕፅዋት ዘር ነው፡

፲፯· "የዘር አምራች" ማለት የዕፅዋት ዘርን የሚያመርት ሰው ነው፡

፲፰· "የዘር አዘጋጅ" ማለት የዘር ማዘጋጃ መሣሪያ በመጠቀም እንደአስፈላጊነቱ ዘርን የሚያደርቅ፣ የሚያበጥር፣ ደረጃ የሚሰጥ፣ በመድኃኒት የሚለውስ፣ እና መለያ ምልክት በማድረግ የሚያሽግ ሰው ነው፡

፲፱· "ኢንስፔክተር" ማለት ማንኛውም ዘር የኢትዮጵያን የዘር ጥራት ደረጃዎችን መስፈርቶች አሟልቶ ስለመገኘቱ በዘር ማምረቻ፣ ማዘጋጃ፣ ማከማቻ፣ እና በጅምላና በችርቻሮ መሸጫ ሥፍራዎች በመገኘት እንዲቆጣጠር በኤጀንሲው ሥልጣን የተሰጠው ሰው ነው።

2. *Definitions*

In this Proclamation, unless the context requires otherwise ;

1) "Board" means the Board of the National Seed industry Agency;
2) "Agency" means the National Seed Industry Agency;
3) "Variety" means sub-division of any kind of plant species that can be clearly differentiated from other varieties of that kind by heritable characters; and that remain stable when reproduced sexually or asexually.
4) "Seed" means true seed, bulbs, tubers, cuttings, nursery plants of field and garden crops or any other plant material used for the propagation of plants;
5) "Prescribed Seed" means any seed to which the provisions of this Proclamation are applicable and which are designated as such by directives to be issued by the Agency;
6) "Certified Seed" means a seed produced in Ethiopia or imported seed which has been certified, by the Agency or other body delegated by the Agency, for conforming to the standards established and which is intended for planting;
7) "Release Committee" means the National Variety Release Committee;
8) "Person" means any natural or juridical person;
9) "Seed Data Base" means the Seed Data Base of the National Seed Industry Agency;
10) "Ethiopian Seed Standards" means national seed standards issued by the Quality and Standards Authority of Ethiopia;
11) "Quality" means the planting value of the prescribed seed;
12) "Objectionable Weed Seeds" means seeds of a specific variety of weed species identified pursuant to the provisions of this Proclamation
13) "Lebel" means any legend, symbol or design applied or attached to package of any seed or which goes with the seed and indicates the quality and quantity of seed;
14) "Seed Processing Plant" means any premises which has adequate facilities for seed processing (drying, cleaning, grading, treating, bagging and labeling, as required) and storage.
15) "Restricted Seed" means seed prohibited from being imported into Ethiopia or exported from Ethiopia or seed put under restriction;
16) "Sub-Standard Seed" means any seed which does not conform to the quality requirements of the Ethiopian Seed Standards;
17) "Seed Producer" means a person who produces seed;
18) "Seed processor" means a person who dries, cleans, grades, treats, bags and labels seed as required by using seed processing machines;
19) "Inspector" means a person authorized by the Agency to inspect seed for conformity to Ethiopian Seed Standards and requirements by visiting seed production, processing and storage premise as well seed as wholesale and retail shops.

ሀ) የዕፅዋት ዘር አምራች ከሆነ በዘር ማምረት ሥራ ላይ በቀጥታ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የሙያ ብቃትና ችሎታ፡ እንዲሁም የሚያመርተው የዕፅዋት ዘር የጥራት ደረጃውን የጠበቀ ለመሆኑ ፍተሻ የሚያደር ግበት ላቦራቶር ማቋቋሙን ወይም በኤጀንሲው ከተወከለ የዘር ጥራት መቆጣጠሪያ ላቦራቶሪ ጋር የጥራት ፍተሻ እንዲያረግለት ውል የፈፀመ ስለመሆኑ ኤጀንሲው ለዚሁ ተግባር ባዘጋጀው ቅጽ ላይ መሙላትና ፊርሞ መስጠት አለበት፤

ለ) የዕፅዋት ዘር አዘጋጅ ከሆነ የሠራተኞቹን የሙያ ብቃትና ችሎታ፡ ብቃት ያላቸው ማበጠሪያና ማሸጊያ መሣሪያዎች እና መጋዘኖች መኖራቸውን በቅጹ ላይ መሙላትና ፊርሞ ማቅረብ አለበት፡

ሐ) የዕፅዋት ዘር ላኪ፡ አስመጪ፡ አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ ከሆነ የሠራተኞቹን የሙያ ብቃትና ችሎታ እንዲሁም ተስማሚ መጋዘን ስለመኖሩ በቅጹ ላይ በመሙላት ፊርሞ መስጠት አለበት፤

፫· የተደነገገ ዘር የማምረት፡ የማዘጋጀት፡ የማስመጣት፡ እና የመላክ፡ የማከፋፈል እና የመቸርቸር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት በሚቀርብ ማመልከቻ ላይ ተገቢውን ለመወሰን ኤጀንሲው ወይም ኤጀንሲው ውክልና የሰጠው አካል የአመልካችን የዘር ማምረቻ፡ ማዘጋጃ፡ ማከፋፈያ እና መቸርቸሪያ ኢንስ ፔክት ያደርጋል።

## ፰· የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚያስከለክሉ ሁኔታዎች

ኤጀንሲው በሚከተሉት ምክንያቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አይሰጥም፡

፩· ቀደም ብሎ የነበረው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰረዘበትና የምስክር ወረቀቱ ከተሰረዘበት ጊዜ ጀምሮ እንደገና እስከተጠየቀበት ጊዜ ድረስ አንድ ዓመት ያልሞላው ሲሆን፡

፪· ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በዕፅዋት ዘር ማምረት፡ ማዘጋጀት፡ ግብይትና ሥርጭት ሥራ ላይ ጥፋት ፈጽሞ በሌላ ሕግ የተፈረደበትና ቅጣቱን ያልጨረሰ ሲሆን፡

፫· በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፮ የተደነገጉትን ያላሟላ እንደሆነ፡

፬· በዚህ አዋጅና ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም በሚወጣ መመሪያ መሠረት የተፈረደበትና ቅጣቱን ያልጨረሰ ሲሆን።

## ፱· ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማግኘት

፩· የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የጠፋበት ወይም የተበላሸበት ማንኛውም ሰው ለኤጀንሲው በጽሑፍ በማመልከት ምትክ ማግኘት ይችላል።

፪· የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የተበላሸበት ሰው ምትክ እንዲሰጠው ሲጠይቅ የተበላሸውን ሠርቲፊኬት ለኤጀንሲው መመለስ አለበት።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የጠፋበት ሰው ምትክ የምስክር ወረቀት መጠየቁን የሚገልጽ የጋዜጣ ማስታወቂያ ኤጀንሲው በአመልካቹ ወጪ እንዲወጣ ባደረገ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተቃዋሚ አለመቅረቡን በማረጋገጥና የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል።

## ፲· የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ

በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለሦስት ዓመት የፀና ይሆናል።

(a) the qualification and capacity of personnel who are directly engaged in seed production, and whether, a laboratory has been established or a contractual agreement has been made with seed quality control laboratory delegated by the Agency to conduct seed quality test, where he is a seed producer;

(b) the qualification and capacity of personnel, availability of suitable seed processing plant cleaning and bagging machine, and appropriate seed stores where he is a seed processor;

(c) the qualification and capacity of personnel and the availability of proper seed store where he is a seed exporter, importer, wholesaler or retailer;

3. For the purpose of appropriate decision on an application for issuance of, the competence assurance certificate to a producer, processor, importer, exporter, wholesaler and retailer of a prescribed seed, the Agency or the body delegated by it shall inspect the production area, processing plant, store and wholesale and retail sales shops which the applicant proposes to use in and about his business.

## 8. *Conditions for Refusal of Certificate of Competence Assurance*

The Agency shall not grant competence assurance certificate to a person for the following reasons;

1) where the previous certificate of competence assurance has been cancelled and the period between cancellation and request is less than one year;
2) where, before the issuance of this proclamation, the applicant has been convicted of an offense under other laws concerned with seed production, processing, marketing and distribution, and has not served the penalty;
3) where the applicant does not fulfill the provisions of Article (6) of this Proclamation; and
4) where the applicant has been convicted and hasn't served the penalty of, an offense under this Proclamation and directives to be issued there under.

## 9. *Obtaining Replacement Certificate of Competence Assurance*

1) Any person whose certificate of competence assurance is lost or destroyed may, upon an application to the Agency in writing, obtain replacement of such certificate.
2) Any person, whose certificate of competence assurance is destroyed, should return the destroyed certificate to the Agency when applying for a replacement.
3) The Agency shall issue a replacement certificate to a person whose certificate of competence assurance is lost, as provided for in Sub-Article /1/ of this Article, within one month after the request for replacement is publicized in a newspaper, by the Agency, at the applicant's expense and, provided that no objection arises and service charge is paid thereto.

## 10. *Period of Validity of Competence Assurance Certificate*

A certificate of competence assurance issued under this Proclamation shall be valid for a period of three years.

፲፩· የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እድሳት

፩· የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ሰው ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ የምስክር ወረቀቱ የሚያገለግልበት ጊዜ ከማብቃቱ በፊት ባለው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ የእድሣት ማመልከቻውን ለኤጀንሲው ማቅረብ አለበት።

፪· ኤጀንሲው የአመልካቹን የሥራ ክንውንና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ሁኔታዎች ከገመገመ በኋላ ማመልከቻው በደረሰው በ፲፭ ቀን ውስጥ የአገልግሎት ዋጋ በማስከፈል የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ያድሳል።

፲፪· የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ስለመሰረዝ እና ስለማገድ

፩· ኤጀንሲው በሚከተሉት ምክንያቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትን ሊሰርዝ ይችላል፤

ሀ) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ያገኘው በማታለል ወይም የሀሰት መረጃ ወይም መግለጫ በማቅረብ መሆኑ ሲታወቅ፤

ለ) ኤጀንሲውን ሳያስፈቅድ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ለሌላ ሰው ካስተላለፈ፤

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ በተደነገገው መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ካላሳደሰ፤

መ) የዕጽዋት ዘር የጥራት ደረጃ መስፈርቶችን ያላሟላ ዘር ሲሸጥ ከተገኘ፤

ሠ) የንግድ ፈቃዱ የተሠረዘበት ከሆነ።

፪· የምስክር ወረቀቱ ከተሰጠባቸው ዝርዝር ሁኔታዎች ውጭ የምስክር ወረቀቱ ባለቤት ሥርቶ ቢገኝ ኤጀንሲው የምስክር ወረቀቱን ሊያግደው ወይም ሊሰርዘው ይችላል።

፫· ኤጀንሲው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን እንደ ሰረዘ የንግድ ፈቃዱም እንዲሰረዝ ለፈቃድ ሰጭው አካል በጽሑፍ ያሳውቃል።

፲፫· መረጃ ስለመያዝና ስለማቅረብ

ማናቸውም የተደነገገ ዘር የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ባለቤት የሆነ አምራች፣ አዘጋጅ፣ አስመጪ፣ ላኪ፣ አከፋፋይ፣ ቸርቻሪ፣

፩· የእያንዳንዱን ማሳ፣ ያመረተውን ዘር፣ ያዘጋጀውን ዘር፣ ያስመጣውን ዘር፣ የላከውን ዘር፣ ያከፋፈለውንና የቸረቸረውን ዘር፣ በዝርዝር መዝግቦ ይይዛል፤

፪· መረጃዎችንና ትንተና የተካሔደባቸውን የዕፅዋት ዘር ናሙናዎች ይይዛል፣ ትንተና የተካሔደባቸውን የዕፅዋት ዘር ናሙናዎችን በተመለከተ ለአንድ ዓመት መያዝ አለበት፣ ናሙናዎችን እንደአስፈላጊነቱ ከዚህም በላይ መያዝ ይችላል።

፫· ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሠረት የያዘውን መረጃ ለኤጀንሲው ይልካል፤ እንዲሁም የኤጀንሲው ኢንስፔክተር መረጃውን ለቁጥጥር በጠየቀ ጊዜ ያቀርባል፤

## ክፍል ሦስት
## ስለ ዕጽዋት ዘር ማምረት፣ ማዘጋጀት፣ ግብይትና ጥራት ቁጥጥር

፲፬· ስለ አመራረት፣ አዘገጃጀትና ግብይት

ማንኛውም በሀገር ውስጥ የሚመረት፣ የሚዘጋጅ፣ ከውጭ የሚመጣና ወደ ውጭ የሚላክ ፣ የሚሸጥና የሚሠራጭ የዕፅዋት ዘር ዝርያው በኤጀንሲው የተመዘገበና ዘሩ የኢትዮጵያን የዘር ደረጃዎች እና መስፈርቶች ያሟላ መሆን አለበት።

11. *Renewal of Competence Assurance Certificate*

1) Every holder of a certificate of competence assurance, desiring to renew the certificate, shall make an application to the Agency in accordance with the form designed for this purpose, within one month before the date of expiry of the said certificate.
2) On receipt of an application for renewal the Agency shall, evaluate the performance of the applicant and other relevant circumstances, and by charging service fee renew the certificate of competence assurance within 15 days period.

12. *Cancellation and Suspension of Certificate of Competence Assurance*

1) The Agency may cancel a certificate of competence assurance on any of the following grounds;
   (a) where the certificate has been obtained by fraud, false documents or misrepresentation as to material particulars;
   (b) where the certificate has been transferred to any other person without prior permission of the Agency;
   (c) where the certificate has not been renewed pursuant to the provisions of Article 11 of this Proclamation;
   (d) where the holder of the certificate of competence assurance has been found selling sub-standard seed;
   (e) where the license for seed business has been cancelled;
2) The Agency may suspend or cancel the certificate if the owner of the certificate has been found using it for other purposes than the terms and conditions it has been issued for.
3) The Agency after having cancelled the certificate of competence assurances shall notify, same in writing to the licensing Authority to cancel his/her seed business license;

13. *Keeping and making Available Records*

Any owner of Competence Assurance Certificate as producer, processor, importer, exporter, distributor and retailer shall:

1) record and keep particulars of each field, seed produced, seed processed, seed imported and exported, and seed distributed and retailed;
2) keep records and seed samples on which analysis have been made keeping. The period for keeping seed samples on which analysis have been made should be one year; keeping samples may also be for more years, as the case may require.
3) transmit to the Agency such records kept as provided under Sub-Articles (1) and (2) hereof and submit same for inspection where requested by the Inspector.

## PART THREE
## Production Processing, Marketing and Quality Control

14. *Seed Production, Processing and Marketing*

Any seed produced and processed locally, or imported or to be exported, or to be sold and distributed in the country shall be a variety registred by the Agency and shall conform to the requirements and seed standards of Ethiopia.

## ፲፭· ስለጥራት ቁጥጥር

፩· ማንኛውም የተደነገገ ዘር አግባብ ያለውን የኢትዮጵያን የዘር ደረጃና መስፈርት ማሟላት ይኖርበታል። የዚህም ተግባራዊነት በኤጀንሲው በኩል ይረጋገጣል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ኢንስፔክተሩ በማናቸውም ማምረቻ፣ ማዘጋጃ፣ ማከማቻ ፣ ማከፋፈያና መቸርቸሪያ ሥፍራዎች ሁሉ በመገኘት ማናቸውም የተደነገገ ዘር ከተወሰነው የኢትዮጵያ የዘር ደረጃ ጋር መጣጣሙን ይቆጣጠራል፣ እንደአስፈላጊነቱም ማሻሻያዎች፣ (ማስተካከያዎች) ፣ እንዲደረጉ ባለቤቱን ይመክራል፣ ባለቤቱም ምክሩን ተቀብሎ አስፈላጊውን ማሻሻያ ፣ (ማስተካከያ)፣ ማድረግ ይኖርበታል።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ማናቸውም የተደነገገ ዘር ከተሻሻለ ወይም ከተስተካከለ በኋላ ባለቤቱ የዘሩን ናሙና ለተጨማሪ ምርመራ ወደ ምርመራው ማዕከል እንዲልክ ኢንስፔክተሩን ሊጠይቀው ይችላል። የዘር መርማሪውም ዘሩ ልዩ ዓይነት ምርመራ የሚፈልግ ካልሆነ በስተቀር የተደነገገው ዘር ከተወሰነው የኢትዮጵያ የዘር ደረጃ ጋር መጣጣሙን ለማረጋገጥ የዘር ናሙናውን ለድጋሚ ምርመራ በመላክ ምርመራ ማዕከሉ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ በ፲፭ ቀን ጊዜ ውስጥ ውጤቱን ለዘሩ ባለቤት መግለጽ ይኖርበታል። የዘሩ ባለቤትም እስከዚያው ጊዜ ድረስ የተደነገገውን ዘር ለዘር አገልግሎት መሸጥ አይችልም።

፬· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ለሚደረገው ተደጋጋሚ የዘር ምርመራ ባለቤቱ ለእያንዳንዱ ለሚደረገው ምርመራ የተወሰነውን ክፍያ ይከፍላል።

፭· ኤጀንሲው በማንኛውም ጊዜ በመጋዘንና በሺያጭ መደርደሪያ ላይ ለሺያጭ የተዘጋጁ ዘሮችን ናሙና በመውሰድ የዘር ደረጃው በዘር ጥራት መግለጫው መሠረት መሆኑን ቁጥጥር ያደርጋል፣ ውጤቱም መግለጫው ላይ ከተመለከተው አንሶ ሲገኝ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል።

## ፲፮· መለያ ምልክት ስለማድረግ

የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በአንቀጽ ፲፭ መሠረት የተመረመረ ማናቸውም የተደነገገ ዘርን የሚሸጥና በአንቀጽ ፲፯ ላይ የተገለጹትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ማንኛውም የተመዘገበ የዘር ሻጭ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባሮች የመፈጸም ግዴታ አለበት፣

ሀ) የአምራቹ ስምና አርማ

ለ) እንደሁኔታው "የተመሰከረለት ዘር የሀገር ውስጥ" ወይም "የተመሰከረለት ዘር የውጭ" የሚል ቃል፣

ሐ) የተደነገገው ዘር የተመረተበት ዓመተ ምህረት እና የተመረመረበት ቀን እና ዓመተ ምህረት፣

መ) የሰብል ዓይነትና የዝርያ ስም፣

ሠ) ሌሎች የዘሩን የጥራት ሁኔታ የሚገልጹ ዝርዝሮችን፣ በመመሪያው መሠረት መያዣው ላይ እንዲታተም ወይም በተወሰነ የዘር ደረጃ መግለጫ ላይ በማይለቅ ቀለም ተጽፈው ከውጭ እንዲለጠፉ እና ከውስጥም እንዲደረጉ ያደርጋል።

## ፲፯· የዘር ሺያጭን ስለመቆጣጠር

፩· ማንኛውም ሰው በብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ላይ በተዘረዘሩት ሁኔታዎች መሠረት የዘር ሻጭ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከሌለው በስተቀር ማናቸውንም የተደነገገ ዘር ለመሸጥ አይችልም።

## 15. *Quality Control*

1) Any prescribed seed shall conform to the requirements of the appropriate Ethiopian Seed Standards and such conformity shall be ascertained by the Agency.

2) The inspector shall, pursuant to Sub-Article (1) of this Article, appear at production, processing, storage, wholesale and retail sites of a prescribed seed and inspect conformity to the designated Ethiopian Standards. He shall also advise the owner of a seed, as may be necessary, to take corrective measures towards improving his seed's standards. The owner of the seed must, pursuant to the advice, make the necessary improvement.

3) Where any prescribed seed has been improved pursuant to Sub-Article (2) of this Article, the owner may request the seed-inspector to send his seed sample to a seed-testing center for further lest. The seed inspector shall notify the owner of the seed, within 15 days starting from the date of receipt of the sample by the seed testing center, the conformity of the prescribed seed to the Ethiopian Seed Standard provided the seed does not require special test. Until such time, the owner cannot offer the prescribed seed for sale.

4) Where repeated testing of such a seed as prescribed in Sub-Article (3) of this Article is made, the owner shall pay such fees as may be prescribed for each test.

5) The Agency may, at any time, take seed samples from stores, wholesale and retail shops and conduct laboratory tests to check whether the sample conforms to the particulars indicated on labels and take legal measures whenever lower test results are observed.

## 16. *Labeling*

Without prejudice to the provisions of this Proclamation, any registered seed seller who sells any prescribed seed which has been tested in accordance with Article 15 and found complying with the provisions of Article 17 has the obligation to cause the printing or stamping with an indelible ink upon such container or upon a specified lable attached thereto and enclosed therein the following particulars in accordance with the directives:

(a) the name of the producer and its emblem;

(b) the words "Certified Seed Local" or "Certified Seed Imported" as the case may be;

(c) year of prduction and the date on and year within which the prescribed seed was tested;

(d) type of crop and name of the variety; and

(e) other particulars specifying the seed quality.

## 17. *Control of Sale of Seed*

1. No person shall sell any prescribed seed unless he has a seed seller's competence assurance certificate issued in accordance with the terms and conditions specified in the competence assurance certificate.

፪· ማንኛውም ሰው ማናቸውንም የተደነገገ ዘር ለመሸጥ ፡ ለሽያጭ ለማስቀመጥ፡ ለሽያጭ ለማቅረብ፡ በዓይነት ለመለወጥ ወይም በሌላ አኳኋን ለማቅረብ የሚችለው፡
   ሀ) የተባለው ዘር ዓይነት እና ዝርያ መሆኑ ሲረጋገጥ፡
   ለ) በዚህ አዋጅ በተወሰነው መሠረት የተወሰደው የዘሩ ናሙና በታወቀ የዘር መመርመሪያ ጣቢያ የተመረመረ እና፡ ዘሩ የኢትዮጵያን የዘር ደረጃ የጠበቀ ሆኖ ሲገኝ፡
   ሐ) መያዣው በአንቀጽ ፲፮ በተደነገገው መሠረት ይዘቱ ግልጽ በሆነና በተወሰነው መሠረት መለያ ምልክት የተደረገበት ሲሆን፡ እና
   መ) የሚሸጠው የተደነገገ ዘር በታሸገ መያዣ ሲሆን ነው።

## ፲፰· ዘርን ስለማረጋገጥ

የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፡
፩· በኢትዮጵያ ውስጥ የተመረተ ዘር ከሆነ የተመሰከረለት የሀገር ውስጥ ዘር መሆኑ ፡ ወይም
፪· የተመሰከረለት ዘር የውጭ መሆኑ፡
በኤጀንሲው ወይም ይህን ሥራ ለመሥራት በኤጀንሲው በተወከለ በሌላ አካል መረጋገጥ አለበት።

## ፲፱· ለውጭ ሀገር የዘር አረጋጋጭ ድርጅቶች እውቅና ስለመስጠት

ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል ኤጀንሲው ውጭ ሀገር ለተቋቋሙ ማናቸውም የኢትዮጵያን የዘር ደረጃዎችና መስፈርቶች የሚያሟሉ ዘሮችን ለሚያረጋግጡ ብቃት ላላቸው የዘር አረጋጋጭ ድርጅቶች እውቅና ሊሰጥ ይችላል።

## ፳· የምስክር ወረቀት ስለመስጠት

፩· ማናቸውንም የተደነገገ ዘር የሚያመርት፡ የሚሸጥ፡ ለሽያጭ የሚያስቀምጥ፡ ለሽያጭ የሚያቀርብ፡ የሚለውጥ ወይም በሌላ አኳኋን የሚያቀርብ ሰው፡
   ሀ) የተባለው ዘር የምስክር ወረቀት እንዲኖረው ከሚያስገድደው የሰብል ዓይነት ውስጥ ከሆነ የምስክር ወረቀቱን ለማግኘት ለኤጀንሲው ማመልከት ይኖርበታል፡
   ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) መሠረት የሚያቀርበውን ማመልከቻ ከተወሰነው ክፍያ ጋር በዝርዝር በተገለጸው መሠረት ማቅረብ ይኖርበታል።
፪· የምስክር ወረቀት አሰጣጥ በሚከተለው ሁኔታ ይፈጸማል፡
   ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ የተመረተ የተደነገገ ዘርን በተመለከተ፡
      ፩· በቅርብ ጊዜ በተዘጋጀው የዝርያ ዝርዝር ውስጥ የተመዘገበ ዝርያ መሆኑን፡
      ፪· የምስክር ወረቀት ከሚሰጣቸው ደረጃዎች ውስጥ መሆኑን ፡
      ፫· የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በተሰጠው የዘር አምራች የተመረተ መሆኑን
      ፬· በዘር አመራረት መመሪያ መሠረት መመረቱን፡
      ፭· በአመራረት ሂደት ወቅት ቁጥጥር የተደረገበት መሆኑን፡
      ፮· በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የተመረመረ መሆኑንና ከአስፈላጊዎቹ የኢትዮጵያ የዘር ደረጃዎች ጋር የተጣጣመ የተደነገገ ዘር መሆኑን፡
   አመልካቹ ለኤጀንሲው ያሳያል።
   ለ) ወደ ኢትዮጵያ የገባ የተደነገገ ዘርን በተመለከተ፡
      ፩· የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በተሰጠው የዘር አስመጪ ወደ ኢትዮጵያ የገባ መሆኑን፡
      ፪· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፬፡ ፲፭ እና ፲፮ ድንጋጌዎች መሠረት የተመረመረ መሆኑን፡

2. Any person may sell, keep for sale, offer for sale, exchange in kind or supply through other means a prescribed seed only where:
   (a) such seed is identifiable to its kind and variety;
   (b) a sample of the seed drawn pursuant to the provisions of this proclamation has been tested at an official seed testing station and found to be in conformity with the Ethiopian Seed Standards;
   (c) its content is clearly indicated on the label as prescribed under Article 16; and
   (d) the prescribed seed offered for sale is in a sealed container.

## 18. *Seed Certification*

Without prejudice to the provisions of this Proclamation, seed shall be certified by the Agency or other delegated body:
1. in the case of seed produced in Ethiopia, that it is a Certified Seed Local; or
2. in the case of foreign seed, that it is a Certified Seed Imported.

## 19. *Recognition of Certification Agencies of Foreign Countries*

The Agency may, for the implementation of this proclamation, recognize any competent certification agencies established in any foreign country to certify seed in conformity with the requirements of the Ethiopian Seed Standards.

## 20 *Issuance of Certificate*

1) A person who produces, sells, keeps for sale, offers for sale, exchanges in kind or supplies through other means any prescribed seed, shall:
   (a) apply to the Agency for the issuance of a certificate if he is producing a crop/crops registered under compulsory certification.
   (b) present the prescribed fee together with his application to be submitted in accordance with Sub-Article (1) (a) of this Article.
2) Issuance of certificate shall be carried out in the following manner:
   (a) Regarding the prescribed seed produced in Ethiopia, an applicant shall show to the Agency that his seed:
      1) is of a registered variety in the current Variety Register;
      2) is of a known certification class;
      3) has been produced by a holder of Competence Assurance Certificate;
      4) has been produced in accordance with the standard seed production procedures;
      5) has been inspected during production process, and
      6) has been tested in accordance with the provisions of this Proclamation and found to be in conformity with the Ethiopian prescribed Seed Standards.
   (b) Regarding the prescribed seed imported into Ethiopia, an applicant shall show to the Agency that his seed:
      1) is imported into Ethiopia by a holder of Competence Assurance Certificate of a seed importer;
      2) is tested in accordance with the provisions of Articles 14, 15 and 16 of this Proclamation;

፫· በኤጀንሲው እና ዘሩ በመጣበት ሀገር ህግ መሠረት እውቅና ባገኘ ድርጅት የተመሰከረለት ዘር ተብሎ የተረጋገጠ ሲሆን፣
፬· በዚህ አዋጅ መሠረት የተመሰከረለት ዘር የሚመረትበትን የኢትዮጵያን የዘር ደረጃ በሚበልጥ ወይም እኩል በመሆን የተመረተ መሆኑን፣
፭· በዕፅዋት ኳራንቲን ደንብ የተደነገጉ የኳራንቲን መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑን፣
፮· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ የተደነገገውን ያሟላ መሆኑን፣
አመልካቹ ለኤጀንሲው ያሳያል።

ሐ) ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሀ) እና (ለ) ስር የተዘረዘሩት ሁኔታዎች በአጥጋቢ ሁኔታ መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ በወሰነው ሁኔታ እና በአዘጋጀው ፎርም እንደሁኔታው "የተመሠከረለት ዘር የሀገር ውስጥ" ወይም "የተመሠከረለት ዘር የውጭ" በማለት ሊያረጋግጥ ይችላል።

መ) ኤጀንሲው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሀ) እና (ለ) መሠረት ማንኛውም ዘር "የተመሠከረለት ዘር" በማለት ካረጋገጠ በኋላ እንደሁኔታው የምስክር ወረቀት በተወሰነው ፎርምና ሁኔታ ለአምራች ወይም ለአስመጭ ይሰጣል።

## ፳፩· ምስክር ወረቀትን ስለመሰረዝ

፩· ኤጀንሲው በዚህ አዋጅ መሠረት የሰጠውን የምስክር ወረቀት የሚሰርዘው፣

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳ መሠረት የተሰጠው የምስክር ወረቀት አስፈላጊ ሁኔታዎችን በተመለከተ የማጭበርበር ተግባር በመፈጸም የተገኘ ሲሆን፣ ወይም

ለ) የምስክር ወረቀቱ ባለቤት የምስክር ወረቀቱ የሚሰጥባቸውን ዝርዝር ሁኔታዎች ያለበቂ ምክንያት ተፈጻሚ ካላደረገና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ መመሪያዎችን ጥሶ ሲገኝ፣

ይሆናል።

፪· ኤጀንሲው የምስክር ወረቀቱን ከመሰረዙ በፊት የምስክር ወረቀቱ የሚሰረዝበትን ሁኔታ በመዘርዘር ለምስክር ወረቀቱ ባለቤት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እንዲደርሰው ያደርጋል፣ አስፈላጊውንም ውሳኔ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይሰጣል።

## ፳፪· የዘር ምርመራ ማዕከላትን ስለማቋቋም፣ ለተቋቋሙት ወይም ለሚቋቋሙት ውክልና ስለመስጠትና የዘር ተንታኞችን ስለመመደብ

፩· ኤጀንሲው የተደነገገ ዘር ምርመራ የሚከናወንባቸውን የዘር ምርመራ ማዕከላትን ያቋቁማል፣ ለተቋቋሙት ወይም ለሚቋቋሙት ውክልና ሊሰጥ ይችላል።

፪· በተወሰኑት ሁኔታዎች መሠረት የዘር ምርመራ እንዲከናወን የዘር ተንታኞች ይመደባል።

## ፳፫· ዘርን ስለማስመርመር

፩· ጥራቱ ያልተመረመረ የተደነገገ ዘር ያመረተ ወይም የያዘ ማናቸውም ሰው ዘሩን ለመሸጥ ከፈለገ ከመሸጡ በፊት በዚህ አዋጅ በተወሰነው መሠረት የዘሩን ናሙና በኤጀንሲው በተቋቋመ ወይም በኤጀንሲው ውክልና ባገኘ የዘር ምርመራ ማዕከል ወይም በራሱ ላቦራቶሪ ማስመርመር አለበት።

፪· ከላይ እንደተመለከተው ባለቤቱ የዘር ናሙና ለምርመራ ከራሱ ላቦራቶሪ ውጭ ወደ ሌላ የምርመራ ማዕከል ሲወስድ ዘሩ ከየት እንደመጣ፣ ዓይነቱንና ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች ዝርዝሮችን ያካተተ መግለጫ ማቅረብ አለበት።

3) is declared as "Certified Seed" by the Agency and by an organization recognized by the laws of the country of its origin;
4) is produced, under conditions equal to or higher than the Ethiopian Seed Standards provided in this proclamation for the production and certification of Certified Seed.
5) complies with the provisions of Plant Quarantine as provided in the Quarantine regulations;
6) complies with the provisions of Article 4 of this Proclamation.

(c) The Agency may, having ascer taindd that the conditions enumerated under Sub–Articles (2) (a) and (b) of this Article have been satisfactorily fulfilled, certify such seed as "Certified Seed Local" or "Certified Seed Imported", as the case may be, in such form and on such conditions as may be decided.

(d) The Agency may, having certified any seed as Certified Seed on the basis of Sub–Articles (2)(a) and (b) of this Artilce, issue to the producer or improter, as the case may be, a certificate in such form and on such conditions as may be decided.

## 21. *Revocation of Certificate*

1) The Agency may revoke the certificate issued under this Proclamation where:
   (a) the certificate issued under Article 20 is found to have been obtained by misrepresentation as to essential conditions; or
   (b) the holder of the certificate has, without reasonable cause, failed to comply with the conditions under which the certificate has been issued or has violated any of the provisions of this Proclamation or directives to be issued pursuant to this Proclamation.
2) The Agency, before revoking the certificate, shall give a written notification stating the reasons for revocation to the holder of a certificate; and shall give the necessary decision within a period of one month.

## 22. *Establishing Seed Testing Centres, Delegating those Established or to be Established and Appointing Seed Analysts.*

1) The Agency shall establish seed testing centres and may delegate those established or to be established testing centers.
2) The Agency shall appoint Seed Analysts to perform seed testing in accordance with the terms and conditions as may be prescribed.

## 23. *Seed Testing*

1) Any person who has proudced or acquired any prescribed seed which has not been tested for quality and intends to sell such seed shall, before selling, have the seed sample thereof tested by a seed testing centre established or delegated by the Agency, or have it tested in his own laboratory in accordance with the provisions of this proclamation.
2) A person who delivers seed samples for testing to a testing center other than his own laboratory shall prescribe the origin, the type of the seed and other particulars as may be determined by directives to be issued by the Agency.

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት፡
   ሀ) አስመርማሪው ከራሱ የምርመራ ማዕከል ውጭ ለሚያደርገው የተደነገገ ዘር ናሙና ምርመራ የተወሰነውን ክፍያ ምርመራውን ለአከናወነው የምርመራ ማዕከል የመክፈል ግዴታ አለበት።
   ለ) የተወሰደው ናሙና በዘር ምርመራ ማዕከል እንደ ደረሰ የተመደበው የዘር ተንታኝ የተወሰነውን መመሪያ በመከተል በናሙናው ላይ ምርመራ አካሂዶ ምርመራው እንዲካሄድለትና የምርመራው ውጤት እንዲደርሰው ለፈለገው ሰው የምርመራውን ውጤትና ለሪፖርቱ አስፈላጊ ናቸው የሚላቸውን ሌሎች ዝርዝሮች በመግለጽ ይሰጣል።

## ፳፬· ስለዘር ኢንስፔክሽንና የዘር ኢንስፔክተር ተግባርና ኃላፊነት

፩· ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል ኤጀንሲው የዘር ኢንስፔክተር ይመድባል።

፪· ኤጀንሲው ለእያንዳንዱ የዘር ኢንስፔክተር የመቆጣጠር ሥልጣን እንዳለው የሚያሳይ የምስክር ወረቀት ይሰጣል።

፫· የዘር ኢንስፔክተሩ በኤጀንሲው በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት ቁጥጥሩ የሚካሄድበት ማንኛውም ሰው በጠየቀ ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተውን የምስክር ወረቀት ማሳየት አለበት።

፬· የዘር ኢንስፔክተሩ፡
   ሀ) ዘሩ የተደነገገ ዘር መሆኑን ለመወሰን እንዲቻል፡
   ለ) የተደነገገው ዘር በዚህ አዋጅ መሠረት ከተወሰነው የጥራት ደረጃ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ለማረጋገጥ ይችል ዘንድ ምርመራ ለማካሄድ፡ እና
   ሐ) በኤጀንሲው በተሰጠው ሥልጣን መሠረት አስፈላጊ ነው ብሎ ላመነባቸው ለሌሎች ምክንያቶች ሁሉ፡

   የዘር ወይም የተክል ናሙናዎችን ሊወስድ ይችላል።

፭· የዘር ኢንስፔክተሩ አዋጁን ለማስፈጸም ሲባል በማናቸውም ተገቢ በሆነ ሰዓት ይህንን አዋጅ በመጣስ የተደነገገ ዘር ንግድ ይካሄድበታል ብሎ የሚያምንባቸውን ማናቸውንም ማሣዎች፡ መጋዘኖች፡ ዘር የጫኑ መኪኖች፡ እና የዘር ማበጠሪያዎችን በመፈተሽ ሥራው ትክክል አለመሆኑን ሲያረጋግጥ እንቅስቃሴውን ማገድ ይችላል።

፮· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የዘር ኢንስፔክተሩ፡
   ሀ) ስለእገዳው ሥራው ለታገደበት ሰው የጽሁፍ ማስረጃ ይሰጣል።
   ለ) ለኤጀንሲው የዕገዳውን ዝርዝር ሁኔታ በመግለጽ ኤጀንሲው በአሥራ አምስት ቀን ጊዜ ውስጥ ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ ያደርጋል።

## ፳፭· ዘር ከውጭ ስለማስገባትና ወደውጭ ስለመላክ

፩· የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የያዘና ዘር የማስገባትና የማስወጣት ፈቃድ ከኤጀንሲው ያገኘ ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም ሰው የተደነገገ ዘርን ለሽያጭ ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት ወይም ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ ለመላክ አይችልም።

፪· ማንኛውም የዘር አስመጪ ወይም ላኪ የተደነገገ ዘርን ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት ወይም ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ ለመላክ የሚችለው፡
   ሀ) ዘሩ የተገደበ ዘር ያልሆነ ሲሆን፡
   ለ) ዘሩ የኢትዮጵያን የዘር ደረጃዎች እና መስፈርቶች ያሟላ ሲሆን፡

3) Pursuant to Sub Article (1) of this Article;
   (a) A person who seeks the testing of a sample of prescribed seed outside his own testing center, shall pay the prescribed fee to the center performing the test.
   (b) Upon receipt of any sample drawn at the seed testing center the official seed analyst shall analyze the sample in prescribed procedure and provide the person who sought the test with the report thereof, the findings therein and such other particulars as may appear necessary for or relevant to the report.

## 24. *Seed Inspection and Duties and Responsiblities of Inspectors*

1) The Agency shall appoint a Seed Inspector for the implementation of this Proclamation.
2) The Agency shall issue to each seed inspector a certificate which shows his authority to inspect.
3) A seed inspector shall produce his certificate of authority given to him pursuant to Sub–Article (2) of this Article, upon request of the person affected by the inspector in the course of exercising any of his powers given to him by the Agency.
4) A Seed Inspector may take samples of any seed or plant for any of the following purposes:
   (a) to determine whether the seed is a prescribed seed;
   (b) to test a seed in order to determine that the prescribed seed conforms to the quality standards prescribed under this Proclamation;
   (c) for such other purposes as he may deem necessary in relation to the powers given to him by the Agency.
5) A seed Inspector may, for the implementation of this Proclamation, at any reasonable time any field, store, vehicle which carries seed and seed processing plant which he has reasonable cause to believe that it is being used in the business of prescribed seed in violation of this Proclamation and when he confirms that the Proclamation has been violated, may suspend the operation of such business.
6) The inspector shall, pursuant to powers given to him under sub–Article (5) of this Article:
   (a) give a written evidence to the person whose business is suspended.
   (b) report to the Agency the details of suspension to enable the Agency to take appropriate measures within 15 days;

## 25. *Import and Export of Seeds*

1) No person shall import into or export from Ethiopia for sale any prescribed seed unless he is a holder of competence assurance certificate and has obtained seed import or export permit from the Agency.
2) any seed importer or exporter shall import into Ethiopia or export from Ethiopia any prescribed seed where:
   (a) such seed is not a restricted Seed;
   (b) such seed conforms to the Ethiopian Seed Standards and requirements;

ሐ) በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ዘሩ መለያ ምልክት የተደረገለትና በመያዣ የታሸገ ሲሆን፣
መ) ዘሩ በዕፅዋት ኳራንቲን የተደነገጉትን የኳራንቲን ደንቦች አሟልቶ ሲገኝ፣
ሠ) ዘሩ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ መሠረት ከፀደቀ፣ ከተሰየመና ከተመዘገበ ዝርያ የተገኘ ሲሆን፣ እና
ረ) የዝርያው ስም ከመጣበት አገር የዝርያ መዝገብ ውስጥ የተመዘገበና በማስረከቢያ ቅጽ ወይም በሌላ ሰነድ ላይ የተገለጸ ሆኖ ሲገኝ ነው።

፫· ዘሩን በአስቸኳይ ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት ከመፈለግ የተነሳ የዘሩን የምስክር ወረቀት ከመጣበት ሀገር መቀበል ካልተቻለ ወይም ወደ ኢትዮጵያ የሚገባው ዘር ለምርምር ተግባር የሚውል ከሆነ ወይም በኤጀንሲው በሚወሰኑ በሌሎች ሁኔታዎች ምክንያት ኤጀንሲው ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባን የተደነገገ ዘር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ረ) ላይ ከተገለጹት ሁኔታዎች ነፃ ሊያደርግ ይችላል።

፬· መንግሥታዊና የግል ምርምር ድርጅቶች ለምርምር ተግባር የዕፅዋት ዝርያዎችን ወደ አገር ውስጥ ማስገባትና ወደ ውጭ ማስወጣት የሚችሉት ከኤጀንሲው ፈቃድ ሲያገኙና የዕፅዋት የኳራንቲን ደንብ ድንጋጌዎች ማሟላታቸው ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

፭· ማንኛውም ሰው በጄኔቲክ ኢንጂነሪንግ ዘዴ ጠባዩን የቀየረ የእፅዋት ዘርን ከውጭ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት የሚችለው የእነዚህን ዕፅዋት ዘሮች አገባብ በተመለከተ ሀገሪቱ በምታወጣቸው ሕጎች መሠረት መስፈርቶችና መመሪያዎች መሟላታቸውን ኤጀንሲው ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ማረጋገጫ ሲያገኝ ብቻ ነው።

፮· ማንኛውም ሰው በሁለተኛው ዙር የማይበቅልና ራሱን የማይደግም ወይም ተርሚኔተር ጂን ቴክኖሎጂ ያለበትን ዘር ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባትና መሸጥ አይችልም።

፳፮· <u>የብቅለት ደረጃው ዝቅተኛ የሆነን ዘር ስለመሸጥ</u>

የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ሰው ማናቸውንም በአገር ውስጥ የተመረተ ያልተበከለና የዝርያ ንጽህና ችግር ያላጋጠመው፣ ነገር ግን ብቅለቱ በመቶኛ ከኢትዮጵያ የዘር ብቅለት ደረጃዎች ፲ በመቶ (ፐርሰንት) ዝቅ ያለ የዕፅዋት ዘር በሚከተሉት ሁኔታዎች መሸጥ፣ ለሽያጭ ማቅረብ፣ ማከማቸት፣ ለሽያጭ ማሳየት ወይም ማከፋፈል ይችላል፣

፩· የዕፅዋት ዘር ዕጥረት በአገር ውስጥ ከፍተኛ መሆኑ ሲረጋገጥ፣ እና
፪· የብቅለት ደረጃውን ያላሟላ የዕፅዋት ዘር ለመሸጥ ከኤጀንሲው አስቀድሞ ፈቃድ የተገኘ እንደሆነ።

፳፯· <u>ጥራቱን/ደረጃውን ያልጠበቀ የዕፅዋት ዘርን ስለማስወገድ</u>

ማንኛውም የዕፅዋት ዘር የኢትዮጵያን የጥራት ደረጃ ያላሟላ መሆኑ ከተረጋገጠ ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከዘርነት ይወገዳል።

፳፰· <u>ስለ ፈቃድ አሰጣጥ</u>

የዕፅዋት ዘር ለማምረት፣ ለማዘጋጀት በጅምላና በችርቻሮ ለመነገድ ማመልከቻ ለፈቃድ ሰጪው ሲቀርብለት ፈቃድ ሰጪው አመልካቹ ከኤጀንሲው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

(c) such seed is labeled and packed in such a container which complies with the provisions of this Proclamation;
(d) such seed complies with the provisions of plant quarantine as provided in quarantine regulations;
(e) such seed is obtained from a variety which was released, named and registered pursuant to Article 4 of this Proclamation; and
(f) where the name of the variety appears in the Variety List of the country of its origin and it is shown on a delivery note or other documents.

3) The Agnecy may exempt, the importation of a prescribed seed, from conditions stated in Sub–Article 2(f) of this Article when it is not possible to receive a certificate from the country of its origin due to the urgency of the need to import the seeds, or where seed is imported into Ethiopia for experimental purposes or due to such other conditions as may be perscribed by the Agency.

4) Research Organizations, both public and private, shall import or export varieties for research purposes only after obtaining permit from the Agency and when these satisfy meeting the requirements of the Plant Quarantine Regulations.

5) Seeds which are genetically modified through genetic engineering, shall be improted only if the Agency receives assurances from the concerned body that these seeds or planting materials are in conformity with the laws issued regarding the importation of genetically modified plants and other pertinent directives.

6) No person shall import and sell seed whose second generation seed cannot germinate or seed which has terminator gene technology.

26. *Selling of Low Germinability Seed*

Without prejudice to the provisions of this Proclamation; any person can sell, offer for sale, stock, exhibit for sale or distribute any locally produced seed which is pure (physically and genetically) but the germination percentage of which is lower by 10% than the Ethiopian Seed Standard, subject to the conditions that:

1) there is an acute shortage of seed in the country; and
2) prior authorization of the Agency is obtained to sell the said seed.

27. *Disposal of Poor Quality (below standard) Seed*

Any seed shall be disposed in accordance with directives to be issued by the Agency, where it is ascertained that the seed does not fulfill the Ethiopian Quality Standard.

28. *Licensing*

The licensing body, upon receipt of application for a license in seed production processing, wholesaling and retailing, shall ascertain that the applicant has obtained a competence assurance certificate from the Agency.

## ክፍል አራት
## የኤጀንሲው የሥራ ድርሻ

**፳፱. የአጽዳቂ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት**

የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የማንኛውም ዕፅዋት አዲስ ዝርያ የሚገመገመው እና የሚጸድቀው አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ተውጣጥቶ በተቋቋመው ብሔራዊ የዝርያ አጽዳቂ ኮሚቴ ነው።

**፴. የኤጀንሲው ተግባርና ኃላፊነት**

ኤጀንሲው ፡ በማቋቋሚያ አዋጁ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ፡

፩. ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡትንም ሆነ በሀገር ውስጥ የሚመረቱትን ዝርያዎች ይወስናል፣

፪. ዓመታዊ የዝርያዎች ዝርዝር (ሬጅስተር) አዘጋጅቶ ያወጣል፣ ሬጅስተሩ ለተጠቃሚዎች መድረሱን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

፫. የዕፅዋት ዘር ማምረት፣ ማዘጋጀት፣ ማስመጣት፣ መላክ፣ በጅምላና በችርቻሮ መሸጥን በተመለከተ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፣

፬. የተደነገገ ዘር ምርመራ የሚከናወንባቸውን የዘር ምርመራ ማዕከላትን ያቋቁማል፣ ለተቋቋሙት ወይም ለሚቋቋሙት ማዕከላት ውክልና ሊሰጥ ይችላል፣

፭. በአዋጁ መሠረት የዘር ምርመራ ያከናውናል፣ የዘር ተንታኞችንም ይመድባል፣

፮. ኤጀንሲው በማንኛውም ጊዜ የተመረተውን፣ የተበጠረውንና ለንግድ የተዘጋጀውን ዘር ናሙና ወስዶ ትንተና ማካሄድ ይችላል፣

፯. ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የኢንስፔክሽን ቡድን አቋቁሞ ኢንስፔክተሮችን ይመድባል፣ ላቦራቶሪዎችን ያቋቁማል፣ ያደራጃል፣ ያስተዳድራል፣ የዕፅዋትን ዘር ጥራት ይመረምራል፣ ይቆጣጠራል፣

፰. ለሚመደበው ማንኛውም የዕፅዋት ዘር ኢንስፔክተር የኤጀንሲው ኢንስፔክተር መሆኑን የሚያረጋግጥ መታወቂያ ይሰጣል፣

፱. ማንኛውም የዘር ንግድ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አግኝቶ በዘር ንግድ ላይ የተሰማራ ሰው ለተባለው ዘር የምስክር ወረቀት እንዲኖረው ፍላጎት ካለውና ካመለከተ ኤጀንሲው ያወጣቸው መስፈርቶች መሟላታቸውን አረጋግጦ የዘር ጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣

፲. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) መሠረት የተሰጠውን የዕፅዋት ዘር የጥራት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የማጭበርበር ተግባር በመፈጸም ወይም የምሥክር ወረቀቱ የሚሰጥባቸውን ዝርዝር ሁኔታዎች ያለበቂ ምክንያት ተፈጻሚ ሳያደርግ ሲቀር ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ መመሪያዎችን ጥሶ ሲገኝ የሰጠውን የዘር ጥራት የምስክር ወረቀት ይሰርዛል፣

፲፩. ኤጀንሲው ለውጭ አገር የዘር አረጋጋጭ ድርጅቶች እውቅና ሊሰጥ ይችላል፣

፲፪. ኤጀንሲው ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ሥልጣኑን በውክልና ለመስጠትና ውክልናው ተፈጻሚ የሚሆንባቸውን ሁኔታዎች ለመወሰን ይችላል፣

፲፫. ኤጀንሲው ለምርምርና ለምርት ተግባራት ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡና ወደ ውጭ ለሚላኩ ዘሮች የማስወጫና የማስገቢያ ፈቃድ ይሰጣል።

**፴፩. የኢንስፔክተር ተግባርና ኃላፊነት**

ኢንስፔክተሩ በኤጀንሲው የሚመደብ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፬ ስር የተመለከቱት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።



## PART FOUR
## The Role of the Agency

29. *Duties and Responsibilities of the Release Committee*

Without prejudice to the provisions of this Proclamation, new variety of any plant is evaluated and released by the National Variety Release Committee (NVRC), composed of members assigned from appropriate bodies.

30. *Duties and Responsibilities of the Agency*

Without prejudice to the powers and duties vested on it under its establishment Proclamation, the Agency:

1) shall decide the type of varieties to be improted or locally produced;
2) shall prepare and issue the annual variety register, follow up and make sure that the register is received by users;
3) shall issue, renew, suspend, and cancel competence assurance certificate in matters related to production, processing, import and export, wholesale and retail of seed;
4) may establish seed testing centers for conducting tests on prescribed seed and may delegate those established or to be established centers;
5) shall perform seed testing by itself in accordance with the provisions of this Proclamation and appoint seed analysts;
6) may take at any time sample for analysis from any place of seed production, processing and from seeds ready for sale;
7) shall by establishing a team for inspection assign inspectors; establish, organize and administer laboratories, and carry out seed quality testing and control activities to enforce this Proclamation;
8) shall issue a certificate of authority to each assigned seed inspector that ascertain he is an inspector of the agency;
9) shall issue a seed quality assurance certificate to any person who, possesses a competence assurance certificate, is engaged in seed business and who desires to have certificate for the said seed and applies for it after assuring that such seed fulfills the Agency's prescribed ceriteria;
10) shall revoke the certificate issued under Sub-Article (9) of this Article, if the certificate issued has been obtained by misrepresentation as to the essential conditions or if the holder of the certificate has failed to comply with conditions under which the certificate has been issued or has violated any of the directives issued in accordance with this Proclamation;
11) may recognize any seed certification agencies established in any foreign country;
12) may delegate its power and decide the conditions upon which the delegation to be exercised for the implementation of this Proclamation;
13) shall give import or export permits for seeds to be imported or exported for research and production purposes.

31. *Duties and Responsibilities of the Inspector*

The inspector shall be assigned by the Agency and shall have the duties and responsibilities specified under Article 24 of this Proclamation.

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፴፪· የመተባበር ግዴታ

በዚህ አዋጅ መሠረት ኢንስፔክተሩ ተግባሩን ማከናወን እንዲችል የሚመለከተው ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት።

፴፫· ስለ አቤቱታ አቀራረብ

፩· በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወሰዱ እርምጃዎች ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው፣ ውሳኔው በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ይግባኙን አግባብ ላለው መደበኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል።

፪· አግባብ ባለው መደበኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ማንኛውም ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ እና አስገዳጅም ነው።

፴፬· ስለቅጣት

፩· ማንኛውም ሰው፣

ሀ) ሆን ብሎ ደረጃውን ያልጠበቀ የዕፅዋት ዘር ወይም ያልተመዘገበ የዕፅዋት ዘር ለሽያጭ ያቀረበ ወይም የሸጠ እንደሆነ ከ፲ ዓመት ባላነሰና ከ፲፭ ዓመት ባልበለጠ የእሥራት ቅጣትና ከብር ፶ ሺ. በማያንስና ከብር ፻ሺ. በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

ለ) በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፯ ከተደነገገው ውጭ የኢትዮጵያን ደረጃዎች ያላሟላ የዕፅዋት ዘር ለሽያጭ ያቀረበ ወይም የሸጠ እንደሆነ ከ፰ ዓመት ባላነሰና ከ፲ ዓመት ባልበለጠ የእሥራት ቅጣትና ከብር ፶ ሺ. ባላነሰና ከብር ፻ሺ. ባልበለጠ መቀጮ ይቀጣል።

ሐ) በዘር ማባዛት፣ ማዘጋጀት፣ ወደ ውጭ መላክ፣ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት፣ ማከፋፈል፣ መቸርቸርና በጥራት ቁጥጥር ሂደት ላይ የማጭበርበር ድርጊት እንዲፈጸም መደለያ ወይም ሌላ ስጦታ የሰጠ ወይም ለመስጠት የሞከረ እንደሆነ ከ፰ ዓመት በማያንስና ከ፲ ዓመት በማይበልጥ እሥራት እና ከብር ፶ ሺ. በማያንስና ከብር ፻ሺ. በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

መ) የከረጢት ስራቱ ደረጃውን ያልጠበቀ መሆኑን እያወቀ በተጠቀሰው ከረጢት የዕፅዋት ዘርን ለሽያጭ ያቀረበ ወይም የሸጠ እንደሆነ ከ፫ ዓመት ባላነሰና ከ፭ ዓመት ባልበለጠ የእሥራት ቅጣትና ከብር ፲፭ሺ. በማያንስና ከብር ፳፭ሺ. በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል።

ሠ) የተወሰደ ናሙና ወይም ለምርመራ የተሰጠ ናሙና በትክክል ምርቱን እንዳይወክል ሆን ብሎ ያዛባ እንደሆነ ከ፪ ዓመት ባላነሰና ከ ፭ ዓመት ባልበለጠ የእሥራት ቅጣትና ከብር ፳ሺ. ባላነሰና ከብር ፴ሺ. ባልበለጠ መቀጮ ይቀጣል።

ረ) በከረጢት ላይ የምልክት አደራረግና የከረጢቱ አስተሻሸግ ደረጃውን ያልጠበቀ ፣ በከረጢቱ ውስጥ ያለው የዕጽዋት የዘር ክብደት መጠን ከተከፈለበት ዋጋ ያነሰ የዕፅዋት ዘር ሆን ብሎ ለሽያጭ ያቀረበ ወይም የሸጠ እንደሆነ ከ፪ ዓመት ባላነሰና ከ፭ ዓመት ባልበለጠ የእሥራት ቅጣትና ከብር ፲ ሺ. ባላነሰና ከብር ፳ ሺ. ባልበለጠ መቀጮ ይቀጣል ።

## PART FIVE
## Miscellaneous Provisions

32. *Duty to co-operate*

Any concerned person, if so required by the inspector, shall be bound to afford all necessary support in order to enable him to exercise his duties under this Proclamation.

33. *Appeal*

1) Any person aggrieved by measures taken pursuant to this Proclamation may appeal to an appropriate regular court within 30 days after he is notified of the decision.
2) Any decision made by a regular court shall be final.

34. *Penalties*

1) Any person who:
   (a) intentionally offers for sale or sells below standard or unregistered seed shall be punished with imprisonment of not less than 10 years and not more than 15 years and with a fine of not less than Birr 50 thousands and not more than Birr 100 thousands.
   (b) offers for sale or sells seed in violation of Article 17 of this Proclamation shall be punished with imprisonment of not less than 8 years and not more than 10 years and with a fine of not less than Birr 50 thousands and not more than 100 thousands.
   (c) gives or offers a gift or any other benefit to cause the commission of fraudulent act on seed production, processing, export, import, distribution, retail sell and quality control process shall be punished with rigorous imprisonment of not less than eight years and not more than ten years and with a fine of not less than Birr 50,000 and not more than 100 thousands.
   (d) knowingly offers for sale or sells seed in bags which do not comply with the standard shall be punished with imprisonment of not less than 3 years and not more than 5 years and with a fine of not less than Birr 15 thousands and not more than 25 thousands.
   (e) intentionally alters the sample drawn or delivered for test and thus resulting in an incorrect representation of the produce, shall be punished with imprisonment of not less than 2 years and not more than 5 years and with a fine of not less than Birr 20 thousands and not more than 30 thousands.
   (f) offers for sale or sells seeds in bags whose labeling and packaging do not comply with the standard and the weight of the seed in the bags is less than the amount paid for it, shall be punished with imprisonment of not less than 2 years and not more than 5 years and with a fine of not less than Birr 10 thousands and not more than 20 thousands.

፴፭· ደንብን እና መመሪያዎች የማውጣት ሥልጣን

፩· የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ደንብ ሊያወጣ ይችላል ።

፪· ኤጀንሲው ይህን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል ።

፴፮· የተሻሩና ተፈጻሚነት ያላቸው ሕጎች

፩· የኢትዮጵያ የዕፅዋት ዘር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፲፮/፲፱፻፹፱ በዚህ አዋጅ ተሽሯል ።

፪· የኢንቨስትመንት እንዲሁም የንግድ ፈቃድና ምዝገባ አዋጆች በዕፅዋት ዘር ሥራ በተሠማራው ሰው ላይ እንደ አግባቡ ተፈጻሚ ይሆናሉ ።

፫· ማንኛውም ሌላ ህግ ወይም የተለመደ አሠራር ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ።

፴፯· አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከግንቦት ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ግንቦት ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

35. *Power to Issue Regulations and Directives*

1) The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.
2) The Agency may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation.

36. *Repealed Laws and Applicable Laws*

1) The Ethiopian Seed Council of Ministers Regulations, No. 16/1997 is hereby repealed.
2) The Investment and Commercial Licensing and Regisrations Proclamations shall be applicalbe to a person engaged in seed business, as the case may be.
3) Other laws or customary practices shall have effect with respect to matters covered by this Proclamation unless they are inconsistent with this Proclamation.

37. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 6th day of June, 2000.

Done at Addis Ababa, this 6th day of June, 2000.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE